# በጥቂቱ በጥቂቱ ይሞላል ሊቃቂቱ

አርአያ ጌታቸው 11-1-17

ይሄ የማንም ታሪክ አይደለም። ይሄ የአገራችን የፖለቲካ ፓርቲዎች የውልደትና እድገት ታሪክ ነው። ከድሮ ጀምሮ አንዲት ኢትዮጵያ የምትባል እድሜ ጠገብ አገር አለች። በዚህች አገር ውስጥም 61 ያህል የፖለቲካ ፓርቲዎች አሉ። እነዚህ ፓርቲዎች በኢትዮጵያ ሲኖሩ ሲኖሩ... እያለ ታሪኩ ይቀጥላል። ያ ታሪክም ሄዶ ሄዶ ቀጥለው የሚያነቡት ሌላ ታሪክ ላይ አደረሰን።

አዎን ቀጥለው የሚያነቡት ታሪክ የአገራችን ተቃዋሚ ፓርቲዎች እንዴት 61 እንደሆኑ እንዴትን እንደበዙ የሚያሳይ አንደኛው የብዜት ታሪካቸው ነው። በዚህ እንጀምር።

መአሕድ የሚባል አንድ ፓርቲ ነበር። በዚህ ፓርቲ ውስጥ የነበሩ ወጣቶች ተፋቅረውና ተሳስበው ሲኖሩ ሲኖሩ ከዕለታት አንድ ቀን ከአመራሩ ጋር ተጋጩ። ግቢም አትግቡ ተባሉ። በጣም ተናደዱ። በእልህ ተነሳስተውም የራሳቸውን ሰው አሰባሰቡና ኢዴፓ የተባለ ፓርቲን መሠረቱ። ከዚያም መኖር ቀጠሉ። አሁንም ሲኖሩ ሲኖሩ በፓርቲያቸው ኢዴፓ መካከል አለመግባባት ተፈጠረ። አለመግባባቱም ቀጠለና በመጨረሻ መኢዴፓ የተባለ ፓርቲ ሊመሰረት በቃ።

መአሕድም አሰላለፉን ቀየረና ከብሄር ፖለቲካ ፓርቲነት ወጣ ብሎ ወደ መላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) እራሱን ለወጠ። ከፈለጋችሁ አሳደገም በሉት። ለእኔ አዘለም አቀፍም ያው ተሸከመ ነው። በዚህ ፓርቲ ስር መቀጠል የፈለጉ ሁሉ ቀጠሉ። ድሮም ውስጣቸው ቁርሾ የነበረባቸው ግለሰቦች ግን ጊዜ ጠብቀው ከ1997ቱ ምርጫ በኋላ ፓርቲውን እሰጥ አገባ ውስጥ ከተቱት። በመጨረሻም ያው እንደተለመደው የተወሰነው ቡድን ከፓርቲው ወጣና ሌላ አዲስ ፓርቲ መሰረተ። የፓርቲውንም ስም ብርሃን ሲል ሰየመው።

ይሄ የ1997ቱ ምርጫ ብዙ ታሪክ ያየንበት እንደነበር ሁላችንም አንዘነጋውም። በተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች መንደርም ብዙ ታሪኮችን አሳይቶናል። እናም ያ ሳይቀናጅ ቅንጅት ተብሎ መጥቶ የነበረው ፓርቲ (ሳይቀናጅ ያልኩት እኔ አይደለሁም። ራሳቸው የፓርቲው ሰዎች ሲበታተኑ በጻፏቸው የግል ታሪኮቻቸው ላይ የገለጹት ጉዳይ ነው) እናም ያ ፓርቲ

ተከፋፈለ። በክፍፍሉ መሰረትም አሁን ያለው ቅንጅት በአቶ አየለ ጫሚሶ ስር ሆኖ ሲቀጥል፤ መኢአድና ኢዴፓ ወደ ነባር ስማቸው ተመለሱ። ሌሎች ደግሞ ሰብሰብ ብለው አንድነትን መሠረቱ።

ፓርቲዎቻችን እንደ አሜባ እየተከፋፈሉ መራባት እጣ ፋንታቸው የሆነ ይመስል አንድነት የተባለው የቅንጅት ክፍልፋይ ፓርቲም በተራው ሰላም ርቆት ችግር ውስጥ ገባ። ችግር ውስጥ የገቡት የፓርቲው ሰዎችም እንደተለመደው ገንጠል አሉና ለምን የራሳችንን ፓርቲ አንመሰረትም ብለው መከሩ። አደረጉትም። ሰማያዊ ፓርቲ የተባለ አዲስ ፓርቲ ሰርተው ወደ ሜዳው ተቀላቀሉ። ይሄ የፖለቲካ ሜዳም አርበ ሰፊ ነውና ሳያቅማማ ተቀበላቸው። እነሱ ግን መታመስ ሲጀምሩ የአንድ ምርጫ እድሜን እንኳን አላሰቆጠሩም ነበር። ዛሬም ድረስ ባልጠራውና በፓርቲው ውስጥ ባለው እሰጥ አገባ ምክንያት ከዛሬ ነገ ሁለት ሆኑ እየተባለ በሽምግልና ሳይቀር እየተደገፉ እንዳሉ አሉ። ከፓርቲዎቹ ታሪክ ተነስተን ካየነው የዚህን ፓርቲ መጨረሻ ለመገመት ዛሬ ቀኑ ረቡዕ መሆኑን የማወቅ ያህል ቀላል ነው። ሰማያዊ ሳይከፈል ከቆየ እስከ አዲስ አበባ ምርጫ፤ ከዘገየ ደግሞ እስከ ምርጫ 2012 ድረስ ይዘልቃል። ከዚያ በኋላ ግን ለሁለት ይከፈላል። ይሄ የእኔ ትንቢት ነው። ይሄ ትንቢቴ ካልሰራ … ያው እንደሰሞኑ ነቢያት ነብይነቴ ይሰረዝ ልበል? አልልም።

ፓርቲዎቻችን ሆይ ኧረ መሰነጣጠቁ ይብቃችሁ! በየዓመቱና በየምርጫ ዘመኑ የአይንህ ቀለም አላማረኝም፤ አንተ እንዲህ ነህ፤ አንተ እንደዚያ ነህ እያላችሁ እንደ አሜባ የምትከፋፈሉበት ዘመን ላይ እንዳልሆናችሁ መናገር እፈልጋለሁ።

እየመጣ ያለው የፖለቲካ እድል በጣም አጓጊና ይበልጥ መጠንከርን የሚጋብዝ ነው። ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች አምርረው ከሚጠሉት ወይንም ከሚቃወሙት ጉዳይ መካከል አንዱ የሆነው የኢትዮጵያ የምርጫ ስርዓትንና ምርጫ ቦርድን ነው። አሁን ደግሞ ይህ ሁኔታ ሊቀየር ከዳር ደርሷል። መንግሥትና ታጋሽ የሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች እያደረጉ ባሉት ድርድር አሁን ያለውን የምርጫ ህግ ከአብላጫ የድምጽ ስርዓት ወደ ቅይጥ ትይዩ ለመለወጥ ከዳር ደርሰዋል። በመርህ ደረጃ ፓርቲዎቹ የአገሪቷ የምርጫ ስርዓት ቅይጥ ትይዩ ይሆን ዘንድ ተስማምተዋል።ይህ የምርጫ ስርዓት ፍጹም ዘመናዊና እንደ ጀርመን ያሉ 30 አገራት እየተጠቀሙበት ያለ ነው። የምርጫ ሥርዓቱ በተለይም የብዙዎችን ድምጽ በማሰማት በኩል ሁነኛ እንደሆነ ነው የየአገራቱ ተሞክሮ የሚያሳየው። እስካሁን ባለው መረጃ 30 አገራት ተግባራዊ አድርገውታል። በቅርቡም ይሄንን የምርጫ ሥርዓት ታይላንድና ሲሪላንካ ተግባራዊ እንደሚያደርጉት አስታውቀዋል።

ቅይጥ ትይዩ የሚባለው የምርጫ ስርዓት የአብላጫ ድምፅ እና የተመጣጣኝ የምርጫ ስርዓትን የሚከተል ሲሆን፤ በአብላጫ ድምጽ ስርዓቱ መሰረት በየምርጫ ክልሉ አንደኛ ሆኖ ያጠናቀቀ ፓርቲ የሚያሸንፍበት ነው። በተመጣጣኝ የምርጫ

ስርዓት ደግሞ ፓርቲዎቹ በየምርጫ ክልሎች ያገኙት ድምፅ ለየምክር ቤቶቹ ወንበር በማካፈል ወንበር እንዲያገኙ ያስችላል። ይህ ማለት በምርጫው ላይ የተወዳዳሪ ፓርቲ ሁሉ በሚያገኘው ድምጽ ልክ ወደምክርቤት ይገባል ማለት ነው። ሁለተኛ ወጣህ ለትንሽ ተሸነፍክ ብሎ ነገር አይኖርም። አንደኛ የወጣው አንደኛ በመውጣቱ ቀጥታ ወደ ምክርቤቶች ሲገባ፤ ሁለተኛ፣ ሶስተኛ ... እና መጨረሻ የወጣው ፓርቲ ደግሞ ያገኛት ድምጽ ተቆጥራና ተሰልታ ባገኛት ልክ ወደ ምክርቤት ሰተት ብሎ መግባቱ አይቀርም።

በዚህ ድርድር መሰረት አሁን የቀረው ፓርቲዎቹ ምን ያህሉ በአብላጫ ድምፅ ምን ያህሉ በተመጣጣኝ ይሁን የሚለውን ምጣኔ መወሰን ነው። እሳከሁን ባለው ሂደት ኢህአዴግ መጀመሪያ ይዞ የቀረበውን የ90/10 (90 ከመቶው የምክር ቤት ወንበር በአብላጫ ድምጽ፤10 በመቶ በተመጣጣኝ) ምጣኔ ወደ 85/15 ዝቅ አድርጎ **እየተከራከረ** ሲሆን። ተቃዋሚዎች በበኩላቸው መጀመሪያ ይዘውት የቀረቡትን የ50 50 ምጣኔ ወደ 60 40 (60 በአብላጫ 40 በተመጣጣኝ) ዝቅ አድርገው የመጨረሻውን ድርድር ለማድረግ ከጫፍ ደርሰዋል። ምን ያህል አድርገው ይወስኑታል የሚለውን አብረን የምናየው ይሆናል።

እኔ ግን ለዚህ ነው ጊዜው የሚከፋፈሉበት ሳይሆን ይበልጥ የሚጠናከሩበት ነው ማለቴ። የንግድ ፈቃድ ይመስል ፓርቲዎች በየጊዜው እየተከፋፈሉና እየተበጣጠሱ ወደ ምርጫ ቦርድ እየሄዱ የፓርቲነት ፈቃድ ማውጣቱን ማቆም አለባቸው። ይልቁንም ፓርቲዎች ተሰባስበው ወገባቸውንም ሸብ አድርገው ገዥ ሆኖ የሚወጣውን ፓርቲ ለመሞገት መሰናዳት የግድ ይላቸዋል። ይህ ቅይጥ ትይይ የሚባለው የምርጫ ስርዓት ካለው ባህሪ የተነሳ ጥምር መንግሥትን ለመመስረት ሁሉ የሚያስገድድ ነው። አሁን ባለው የተበጣጠሰና የተዳከመ አካሄድ እውነት እናውራ ከተባለ ኢህአዴግ ከማን ጋር ጥምር መንግሥት ሊመሰርት ይችላል? በእኔ እምነት ከማንም። ስለሆነም ተቃዋሚዎች ሆይ ጠንክሩማ።

ከዚህ ድርድር መለስ ደግሞ እንደ አጠቃላይ ስለመጪው የአገራችን ፖለቲካ ማለት የምፈልገው ጉዳይ አለኝ። ይህ የምርጫ ስርዓት እውን ሆኖ ተግባራዊ ሲደረግ የአገራችን ፓርላማ በትክክልም የተለያዩ ሀሳቦች የሚደመጡበት ሞቅ ያለ ክርክርም የሚደረግበት እንደሚሆን ምንም ጥርጥር የለኝም። በተለይም ውሳኔ በሚተላለፍባቸው ቀናት የአንድ አባል መቅረት እዳው ብዙ ስለሚሆን አሁን እንዳለው ሲያሻቸው የሚመጡ ሲያሻቸው የሚቀሩ አባላት አይኖሩም ማለት እችላለሁ። አሁን ባለው ሁኔታ ከ547 የምክር ቤት አባላት በየስብሰባው የሚገኘው አባል ብዛት ከ347 የሚዘል አልሆነም። ለምሳሌ ሰሞኑን ጠቅላይ ሚኒስትሩ በተገኙበት ስብሰባ ላይ እንኳን ምክር ቤቱ በተለይ ከአፈጉባኤው መቀመጫ በስተቀኝ ያለው ክንፍ ባዶ ሆኖ

ይታይ ነበር። በተዘዋዋሪ ባገኘሁት መረጃ በዕለቱ የተገኘው የምክር ቤት አባል ብዛት 370 ነበር። 177 አባላት ቀርተዋል፤ ወይንም በአንድም በሌላም ምክንያት አልተገኙም ማለት ነው።

ይህ አይነቱ አካሄድ በአዲሱ የምርጫ ስርዓት በሚቋቋመው ምክር ቤት ውስጥ ይኖራል ማለት ዘበት ነው። እንዳሻው መቅረትም ኪሳራው ብዙ ስለሚሆን ፓርቲዎች በየምክርቤቱ የሚወከሉ አባሎቻቸውን ወጥረው እንደሚይዙ ጥርጥር የለኝም። ያኔ አሁን ካለውም በላይ ለአገርና ለህዝብ የሚጠቅም ነገር ጠብ ማለቱ አይቀርም። በተለይም ምርጫ 2012 በአዲሱ የምርጫ ስርዓት የሚካሄድ ከሆነና ተቃዋሚዎች ባገኙት ልክ ወደ ምክርቤቶች ከገቡ፤ የተቃዋሚዎች መንደር ፖለቲካ ይነቃቃል። በዚህም በአገር ውስጥ በፓርቲ ተደራጅቶ ትግል ማድረግ አይቻልም ብለው ተገቢ ባልሆነ መንገድ ራሳቸውን ከፖለቲካ አግልለው የኖሩ አቅም ያላቸው ፖለቲከኞችም ሆኑ ወጣቶች ወደሚመስላቸው ፓርቲ መምጣታቸውና መቀላቀላቸው አይቀርም። ይሄ ደግሞ አሁን ያለውን የመድብለ ፓርቲ ፖለቲካ ስርዓት ይበልጥ ያጎለብተዋል፤ መንግሥት የሚሆነው ፓርቲም ያለእረፍት እንዲሠራ ያስገድደዋል።

ይህ የሚሆነው ግን ከምንም በላይ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በአንድም በሌላም እዚህም እዚያም እየታዩ ያሉ ሁከቶችንና ግጭቶችን እስከ ምርጫ 2012 መልክ ማስያዝ ከተቻለና ሰለማችንን ማስጠበቅ ከቻልን ብቻ ነው። ሰለማችን በእጃችን ነውና መወሰድ ያለበት እርምጃ ሁሉ ተወስዶ እዚያ ከደረስን በየምርጫ ዘመኑ በጥቂቱ በጥቂቱ እየተጓዝን ከዴሞክራሲው ጥግ እንደርሳለን። እኔም እኮ ለዚህም ነው ጥቂት በጥቂት ይሞላል ልቃቂት ማለቴ። አበቃሁ!